የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ
Ethiopian Pharmaceuticals Supply Agency

ቀን Date ጳጉሜ 04 2013
ቁጥር Ref. No. 00ነ20/06/257/04

**በጨረታ ቁጥር NCB/EPSA6/RDF-R/PH/01/21 ለመሳተፍ የጨረታ ሰነድ ለገዛችሁ ተጫራቾች በሙሉ**

ጉዳዩ፡ <u>የጨረታ ሰነድ ማስተካከያን ይመለከታል</u>

ከላይ የተጠቀሰዉ ጨረታ ቁጥር የጨረታ ሰነዱ ላይ በክፍል 3(የጨረታ ግምገማ ዘዴና መስፈርቶች-የቴክኒካል መስፈርቶችን በተመለከተ) እንዲሁም በክፍል 6(የቴክኒክ ዝርዝር አጠቃላይ ፍላጎቶች ላይ አንድ መድኃኒት የተካተተ በመሆኑ) መስተካከያ የተደረገ መሆኑን እየገለፅን ማስተካከያዉም ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ማድረጋችንን እናሳዉቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አባሪ፡ 2 ገፅ

ግልባጭ፡

- ለግዥ አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለፋይል

ኢ.መ.አ.ኤ.

Tel. 011-275 17 70 | 011-275 06 74 | 011-276 06 76 | 011-276 32 65 (Director General Office) | 011-276 32 73 | 011-276 32 66
011-275 93 24 (HR) | 011-276 32 72 (Distribution Directorate) | 011-276 32 68 (Fund Directorate) | Fax. 011-275 25 55 | 011-155 32 77
E-mail: info@epsa.gov.et | P.O.Box- 21904, Addis Ababa, Ethiopia | www.epsa.gov.et

## በክፍል 3- የቴክኒካል መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የተደረገ ማስተካከያ

1.2 የተጫራቹ ቴክኒካል ብቃት፣ ክህሎትና የሥራ ልምድ (የተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 16)

ሀ. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት መድኃኒት በተቆጣጣሪዉ መ/ቤት የተሰጠ የታደሰ የማምረቻ ፍቃድ እና የመልካም አመራረት ስርዓት የእፎይታ ጊዜ ደብዳቤ (GMP exmption letter from EFDA) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተጫራቾች ከሀገር ዉጭ የተመረተዉን መድኃኒት ለማቅረብ የሚወዳደሩ ከሆነ በተቆጣጣሪዉ መስሪያቤት(ማለትም በኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን) የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት (product registration certificate) ጨረታዉ ከመዘጋቱ በፊት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለ.በተጫራቾች የሚሰጠዉ መድኃኒት የመጠቀሚያ ጊዜ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን ይኖርበታል፡፤

ሐ. የምርቱ ስም፣ ጥንካሬዉና ይዘቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸዉ መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፤

መ. የጨረታ ግምገማ ሲደረግ የተጫራቾቹን የሁለት ዓመት (ሰኔ 30, 2011 እስከ ሰኔ 30, 2013 ዓ.ም) አፈጻጸም ግምት ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን አፈጻጽማቸው 50 በመቶና በላይ የሆኑ ተጫራቾች ብቻ የውድድሩ አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡

ሠ. ከተጫራቾች ጋር የሚገባው ውል ከታች "አሸናፊ ጨረታን ስለመወሰን" በሚለው ስር በ2.7 በተመለከተው መጠን መሠረት ይሆናል፡፡

**NB:**

- አዲስ ወደ ገበያ ለሚገቡ ተጫራቾች ወይም ከአሁን በፊት በነበሩ ጨረታዎች ተጨራቹ በተጠቀሰው መድኃኒት አሸንፎ የማያውቅ ከሆነ በፊደል መ ላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ተፈፃሚ የማይሆኑ ሲሆን ነገር ግን ተጫራቾቹ በመጀመሪያ 50 በመቶ መጠን የሙከራ ትዕዛዝ የሚሰጣቸው ሲሆን ቀሪው መጠን ደግሞ ምርቶቹን አስገብተው ሲጨርሱ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡
- የሀገር ውስጥ አምራቶች የ25 በመቶ የዋጋ ከለላ ተጠቃሚ ለመሆን በአገር ውስጥ 35 በመቶ እሴት ስለማከላቸው ከተረጋገጠ ኦዲተር የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- በአንድ ምርት ላይ ከአንድ በላይ ተጫራቾች ከተሳተፉ እና የቅድመ ምዘናዉንና ቴክኒክ ምዘናዉን በማለፍ ወደ ዋጋ ዉድድር ከቀረቡ

## በክፍል 6- የቴክኒክ ዝርዝር አጠቃላይ ፍላጎቶች ላይ የተካተተ(የተጨመረ) መድኃኒት

| ተ.ቁ | መገለጫ | መለኪያ | ብዛት | የመጠቀሚያ ጊዜ (shelf life) | መዳረሻ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 65 | Lithium Carbonate 300mg tablet | 10x10 | 924 | ≥ 2 years | EPSA Addis Ababa Warehouse |